# ማክቤዝ

ከዊሊያም ሼክስፒር

ጸጋዬ ገብረ መድኅን

እንደተረጐመው



KR
2.33

# ማክቤዝ

UNIVERSITY
LIBRARY

ዊሊያም ሼክስፒር

እንደጻፈው

ጸጋዬ ገብረ መድኅን

እንደተረጐመው

822.33

ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

፲፱፻፷፪ ዓ. ም.

አዲስ አበባ

OXFORD UNIVERSITY PRESS, ELY HOUSE, LONDON W. 1.

*Glasgow New York Toronto Melbourne Wellington*
*Cape Town Ibadan Nairobi Dar es Salaam Lusaka Addis Ababa*
*Delhi Bombay Calcutta Madras Karachi Lahore Dacca*
*Kuala Lumpur Singapore Hong Kong Tokyo*

OXFORD UNIVERSITY PRESS, P. O. Box 1024, ADDIS ABABA, ETHIOPIA

# MACBETH

© OXFORD UNIVERSITY PRESS 1972

መብቱ ፡ በሕግ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
በ፵፪ኛ ዘመነ መንግሥት ታተመ ።

**Printed by Commercial Printing Press**
**and**
**Published by Oxford University Press**

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| መግቢያ | | (መ) |
| ገቢር አንድ | | ገጽ ፩ |
| | ት፡ ፩ | ፩ |
| | ፪ | ፪ |
| | ፫ | ፭ |
| | ፬ | ፲ |
| | ፭ | ፲፪ |
| | ፮ | ፲፭ |
| | ፯ | ፲፯ |
| ገቢር ሁለት | | ፳ |
| | ት፡ ፩ | ፳ |
| | ፪ | ፳፪ |
| | ፫ | ፳፯ |
| | ፬ | ፴፪ |
| ገቢር ሦስት | | ፴፭ |
| | ት፡ ፩ | ፴፭ |
| | ፪ | ፵ |
| | ፫ | ፵፩ |
| | ፬ | ፵፰ |
| ገቢር አራት | | ፶፩ |
| | ት፡ ፩ | ፶፩ |
| | ፪ | ፶፬ |
| ገቢር አምስት | | ፶፱ |
| | ት፡ ፩ | ፶፱ |
| | ፪ | ፷፩ |
| | ፫ | ፷፪ |
| | ፬ | ፷፯ |

ለፈደል ፡ ለግዕዝ ፡ ለግሥ እርባታ ፡ ለአገባብ ፡ ለሰዋስውና ፡
ለአማርኛ ቅኔ መምህራኔ ፦

፩. ለአለቃ ብሥራት ወልደ ሥላሴ

፪. ለመምህር ወልደ ማርያም ወርቁ

፫. ለአለቃ ማእምር ዮሐንስ

፬. ለአለቃ ፈለገ ሰላም ገብረ መስቀል

፭. ለአለቃ ጽጌ ገብረ ኪዳን

መታሰቢያ ይሁን ።

# ገቢር አንድ

## ት*፡ ፩

ነጐድጓድና መብረቅ ሲያስተጋባ ሠለስቱ የቃልቾች ርኩስ መናፍስት ይሰማሉ—

ያንደኛይቱ ቃልቻ
መች ይሆን የምንገናኝ ?
ሶስታችን የምንገናኝ ?
የዝናብ ቸንፈር ወርዶ ፡ ወጨፎው ብርሃንን ሲገሥ ?
ቅዝቃዜ ባየር ሲነግስ ?
ሰማይ በመብረቅ ሲታረስ ?
ነጐድጓዱ ምድርን ሲያፈርስ ? . . .
መች ይሆን የምንገናኝ ?

የሁለተኛይቱ ቃልቻ
ጀግና ለጀግና ሲዋቃ ፤
መስከ በደም ተጥለቅልቃ ፤
የምሱን ተፍቶ ሲያበቃ ፤
ጥምብ አንሳ ባስከሬን ሲዋኝ ፤
ኮከብ ቆጥረን እንገናኝ ።

የሶስተኛይቱ ቃልቻ
ያማ ጀምበር ስትጠልቅ ነው ።

ያንደኛይቱ ቃልቻ
ስፍራውን የት ላይ እናርገው ?

የሁለተኛይቱ ቃልቻ
ቁጥቃጦው ነው የሚሻለው ።

የሶስተኛይቱ ቃልቻ
ማክቤዝ እዚያ ነው እሚያረፍደው !

ያንደኛይቱ ቃልቻ
እኔ እግረ ሸረሪት አልቀር ።

---

* ት ፡ ትዕይንት

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

እንዴት ! ለምን ? ለምን ?

**ማክቤዝ**

እንዱ ነፍሰ ገዳይ ያዝ ሲል ፣ ሌላው በእንቅልፉ ሳቅ ይዞት
ያ በጩኸት ፣ ይኸ በሳቅ ፣ እንዱ ሌላውን ቀስቅሶት
እንደመባነን አሉና ፣ ወዲያው ሁለቱም በጸሎት
እማተቡና ጭጭ አሉ ፣ ሕሊናቸው እንቅልፍ ውጦት . . . .

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

ሰው ባኖ ደሞ ቢተኛ ፣ አዲስ ነገር ነው ተባለ ?

**ማክቤዝ**

ይኸን ነፍሰ ገዳይ እጄን ፣ ሲያዩኝ ዓይኑ ደም መሰለ ፤
አይቶ እግዚአብሔር ሰውረን ሲል ፣ ሌላው ዓሜን ዓሜን አለ ።
ፍርሃታቸውን ፀነስኩት ፣ እጄን ዓይቶ ሲል ፣ ሰውረኝ !
ሌላው ደጋግሞ ዓሜን ሲል ፣ እኔ ዓሜን ማለት እቃተኝ ።

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

እኮ በቃህ አትብረክረክ ፤ እስከዚህ አትሰቃይ ተወው !

**ማክቤዝ**

እስቲ ዓሜን ማለት ያቃተኝ ፣ ኧረ ምክንያቱ ለምን ነው ?
የእግዚአብሔር ቡራኬ እንደዚያ ፣ እጅግ ባስፈለገኝ ሰዓት
ዓሜን ካፌ አልወጣ ብሎኝ ፣ ጉሮሮዬን ተናነቃት ።

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

ማክቤዝ ፣ ይኸን እኮ ድርጊት ፣ አይገባም ማሰላሰል
ዕብዶች እንድንሆን ካልፈለግህ ፣ ሕሊናችንን በማቁሰል ።

**ማክቤዝ**

ድምፅ የተሰማኝ መሰለኝ ፣ እንዲህ ብሎ የሚለፍፍ . . . .
ከእንግዲህ እንቅልፍ አትኖርም ፣ እንቅልፍ ሞታለች በግፍ
ማክቤዝ እንቅልፍን ገደላት ፣ ሰላማዊይቱን እንቅልፍ ፤
ሥጋት ያሳሳትን መንፈስ ፣ በእረፍት እቅፉ እምታድስ
ለየዕለቱ ጥረት ፣ ልፋት ፣ እፎይታን የምትለግስ
ድካም ያደረቀው ጫንቃን ፣ በቅዱስ ውሀ እምታርስ
ማወናበድ ላቆሰላት ፣ አእምሮ ሰላም የምትሰጥ
የሕይወት ሕብስተ መና ፣ የእናት ግብሯ እማይለወጥ
ከእንግዲህ እንቅልፍ የለችም ፣ የእረፍት አድባር አጣች መቅኖ
ማክቤዝ እንቅልፍን ገደላት ፣ በእኩለ ሌሊት አፍኖ . . . .



**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

ምን ማለትህ ነው እባክህ ?

**ማክቤዝ**

እዋጅ ! እዋጅ ! ብሎ ጮኸ ፣ ጮኸ ፣ ልሳኑን እትፍጥኖ
ከእንግዲህ ይቺ ቤት በቃት ፣ የላትም የእንቅልፍ መቅኖ ።
የግላሚስ ገዥ ሲገድላት ፣ የካውዶር ገዥ ከቶ አይተኛም
የእንቅልፍ ሕይወት አጥፊው ማክቤዝ ፣ አያገኝ የእንቅልፍን ሰላም . . . .

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

ማን አባቱ ነው እንዲህ ያለው ? . . . ማነው ይኸነን ያወራ ?
ወይስ መንፈስህ ሰንፋ ነው ፣ ማክቤዝ የጀግኖቹ አውራ ?
ምነው ጠንካራ መንፈስክን ፣ ሠራዊት ሁሉ ሲያምንባት
በስሜት ማዕበል ተቀዝፋ ፣ እንድትዋልል ፈቀድህላት ?
ተው ቁልቁል አትንሸራተት ፣ ስሜትህ ትታገድ በዘብ . . . .
ሂድ ውሀ ብጤ ፈልገህ ፣ ይኸን ደም ከእጆችህ እጠብ ፤
ደሞስ ይኸኛውን ጩቤ ፣ ለምን ከዚያ አመጣኸው ?
ኧረ ሂድ ውሰድ መልሰው !
ካንቀላፉት አልባሾች ጉን ፣ እንደነበረ አኑረው !
ልብሳቸውን በደም ለውስ ፣ ግፉ የነሱ እንዲመስል . . . .
ማክቤዝ ውሰድ እኮ ነው እምል ?

**ማክቤዝ**

እኔ አልሄድም ! በቃ አልሄድም !
ከዚች ሥፍራ ዝር አልልም !
የማይቀርልኝ ድርጊቴን ፣ እንዴ አድርጌ ወጥቶልኛል
ዳግመኛ ባይኔ ምስክር ፣ ማስተዋሉ ይቀፈኛል ፤ . . . ይቀፈኛል !

**እመቤት ሆይ ማክቤዝ**

ስጠኝ ለኔ !
ይብላኝለት ላንተስ ወኔ !
የሞተና ያንቀላፋን ፣ ማስተዋል ፎቶግራፍ ነው
የጋኔልን ስዕል ማየት ፣ ለልጅ ዓይን ነው ሚቀፈው . . . .
ከዳንካን ቁስል እስካሁን ፣ ደሙ ሁሉ ወርዶ ባያልቅ
የነዚያን የእንቅልፋሞች ፊት ፣ ዘግኜ ነው እምለቀልቅ . . . .
ያረፈባቸው ዓይን ሁሉ ፣ ግፉን በነሱ እንዲያጸድቅ ! . . .

—ትወጣለች ፡ በር ይንኳኳል—

**ማክቤዝ**

ከየት ነው በር የሚደበደብ ! . . .
ኧረ ምነው ድምፅ አስጠላኝ ፣ ስሰማው የምንገበገብ ?

ቀኑን ...ጂ ፣ አሁን ጀመረ ፣ ወደ እስኮን ዶብር መግሥገሥ
ቀኑን በጉዞ ላይ ውሎ ፣ እዚያው ተቀብቶ ለመንገሥ ።

**ሮስ**
የጃንሆይስ አስከሬን ?

**ማከዳፍ**
ሄዶ ወደ ኮልም ዶብር
ከአባቶቻቸው መቃብር ።

**ሮስ**
አንተስ ወደ እስኮን ነው እምትሄድ ?

**ማከዳፍ**
የለም ፣ ፊፈ ነው እምሄድ
እዚያው እዘመዶቼ ዘንድ ።

**ሮስ**
እኔስ እስኮን ነው እምሄድ

**ማከዳፍ**
ጉዞህን የሰላም ያርገው ፣ ከዚህ ካዲሱ አቀማመጥ
አሮጌው መደረቢያችን ፣ ቀለል ብሎ ባይቀመጥ . . . .
እስቲ እንግዲህ እሱ ያውቃል ፣ በደህና ይግጠመን ጌታዬ ።

—መጋረጃ ይጣላል—

# ገቢር ሦስት

## ት፡ ፩

—ባንቆ ይገባል—

**ባንቆ**
ላንተስ የሕልማችን ውጤት ፣ እንደማይሆን ሆኖም ሆነህ ፣
በንግርት ሆነ በትንቢት ፣ አልመህ ሆነ ወይ ቃኘተህ
አይደፈር ድፍረት ደፍረህ ፣ አይደረግ ድርጊት አርገህ ፤
ታዲያ እኮ ፣ . . . ልጅህ ይነግሣል ፣ እኔ እሆናለሁ ሥሩ
ልጅ ልጆም ይነግሣል ብሏል ፣ አላለቀ ተአምሩ ።
አንተም ከገኘርነት አልፈህ ፣ እንግዲህ ይኸው ነግሠሃል
ምንም የቀረብህ የለ ፣ አንተ ድረስ ሁሉም ጸድቋል
ታዲያን ለኔስ የተቸው ቃል ፣ ይፈጸማል ወይ ይቀራል ?
ብቻ እንደንግርቱ ቃል ፣ ያንተ ጉዳይ ከሠመረ
የኔም ልጅ ሳይነግሥ አልቀረ ።
መለፍለፍ ይቅርብኝ አቦ
እስከዚያው አፌን በዳቦ ።

—ማክቤዝ ንጉሥ ፣ እመቤት ሆይ ማክቤዝ ንግሥት ሆና ፣
ሌኖክስና ሮስም ካጃቢዎች ጋር ሆነው ይገባሉ—

**ማክቤዝ**
ባንቆ አሁን መሄድህ ነው ?

**ባንቆ**
አዎን መሄዴ ነው ጃንሆይ ፤

**ማክቤዝ**
ማታ ለበዓሉ ግብዣ ፣ ደርሰህ ትመለስ የለም ወይ ?

**ባንቆ**
እንዴታ ፣ እመለሳለሁ ።

**ማክቤዝ**
እኔም እጠብቅሃለሁ ፣

ለሞትህ ነው የምትቀርበኝ ! . . .
ተጠበቀኝ ! ተጠበቀኝ ! . . .
ሴት እምጣ የወለደችው ፣ ማንም ወንድ እኔን አይጥለኝ !

ማክዳፍ

እንግዲያስ ትንቢትክን ዋጣት ፣ ረክሳብሃለች ንግርትህ !
መጥፊያህ ሆናለች መተትህ !
እንግዲያስ ቃልህ ትንቅህ ! . . .
እናቴ አላማጠችኝም ፣ በአዋላጅ ኃይል ተመንጥቄ
በግድ የተወለድኩ ነኝ ፣ ከማሕፀኗ ተበጭቄ !
ዋጣት መጥፊያህ ናት ንግርትህ !
የገዛ ቃልህ ትንቅህ ! . . .
ቀጠሮ አላት የእጇ ካራ
ከዚህ ከዐይንህ ብረት ጋራ !
የልጅ ደም ካፈነው ሞራ ! . . .

—ማክቤዝ ይበረግግና ዙፋኑን ወርውሮ እያፈገፈገ ይወጣል—

ማክቤዝ

ማክቤዝ ነኝ ፣ ማክዳፍ አትርሣ
የምራመድ ባንተ ሬሣ !
እንኳን ላንተ ፣ ለሰይጣንም ፣ ለጋኔልም አልደነብር
ተጠንቀቅ ፤ የከንዴ ጋሻ ፣ ትሆንሃለች መቃብር ! . . .

—ማክዳፍ ተከታትሎት እየወጣ—

ማክዳፍ

ዋጣት ፣ ረክሳለች ንግርትህ
የገዛ ቃልህ ትንቅህ !
ቀጠሮ አላት የእጇ ካራ !
ከዚች ከዓይንህ ብሌን ጋራ . . . .
የልጅ ደም ካፈናት ሞራ . . . .

—ተከታትለው ይወጣሉ ። ማክቤዝ ይሞታል ። ወዲያው ማልኮልም ከአጃቢዎቹ ጋር ይገባና የወደቀውን ዙፋን ቀና ሲያደርግ መጋረጃ ይጣላል—

ተ ፈ ጸ መ ።

Not to be taken out
of the Library

ETHIOPIAN COLLECTION
NOT TO BE TAKEN
FROM THE DEPARTMENT

ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

አዲስ አበባ